Australian Government

Department of Home Affairs

# Privacy notice

# ስለ ግላዊነት ማሳሰቢያ

Form

1442i AMH

AMHARIC

Department of Home Affairs (የሆም አፌርስ መምሪያ (መምሪያው) ለአውስትራሊያ ደንበር ጥበቃ ሀይል ያካተተ ነው። ከግለሰቦች ስለግላዊ የሆነ መረጃ መምሪያው በሚወስድበት ጊዜ በአንዳንድ የግለሰብ ጉዳዮች ላይ በተመለከተ ማሳሰብ እንዳለበት
The *Privacy Act 1988* (*የብቻነት አንቀጽ ህግ 1988 ዓ.ም*) ይጠይቃል። ይህ ቅጽ እነዚህን ጉዳዮች የሚያሳውቁበት ነው።

## ግላዊ መረጃ ምንድ ነው?

በግላዊነት አንቀጽ ህግ እንዳቀረበው ግላዊ መረጃ ማለት አንድን ግለሰብ በአግባቡ ለመለየት ሲባል የሚወሰድ ግላዊ መረጃ ነው።

እንዲሁም በግላዊ ሚስጥር አንቀጽ ህግ መሰረት የሚካተት አንዳንድ ስሜት የሚነኩ ግላዊ መረጃዎች በመምሪያው በኩል ጥበቃ እንደሚይደርግ፤ ይህም ስለ ግለሰብ ጎሳ ዘር ወይም ስለ ትውልደ ጎሳ፤ ጾታዊ አገላለጽ ወይም ተግባር፣ ስለ ወንጀል ሪኮርድ፤ የጤና መረጃና የባዮመቲክስ/biometric መረጃ፣ ስለ ሙያተኛ ወይም የንግድ ሥራ ማህበር አባል መሆን፣ ስለ ሃይማኖታዊና ፍልስፍና እምነት ወይም የፖለቲካ ማህበር አባል በመሆን ያሉት መረጃዎች ይሆናል።

በመምሪያው የህግ አወጣጥ ላይ ዋናው ክፍል *Migration Act 1958* (the Migration Act) (*የማይግሪሽን ስደተኛ አንቀጽ ህግ 1958* (የማይግሪሽን አንቀጽ ህግ)) *Customs Act 1901* (the Customs Act) (*የጉምሩኽ ቀረጥ አንቀጽ ህግ 1901* (ጉምሩኽ ቀረጥ አንቀጽ ህግ))፤ *Immigration (Guardianship of Children) Act 1946* (the IGOC Act), *(በኢሚግሬሽን (የህጻናት ማሳደግ ምግባር) አንቀጽ ህግ 1946* (the IGOC Act)) *Excise Act 1901* (the Excise Act) (*ከአገር የመውጫ አንቀድ ህግ 1901* (ከአገር የመውጫ አንቀድ ህግ))፤ *Australian Border Force Act 2015* (the Border Force Act) (*የአውስትራሊያ ደንበር ጥበቃ ሀይል አንቀጽ ህግ 2015* (የድንበር ማስገደጃ ሀይል))፤ ናይ *Maritime Powers Act 2013* (Maritime Powers Act) (*የማሪታይም ሥልጣን ሀይል አንቀጽ ህግ 2013* (ማሪታይም ሥልጣን ሀይል አንቀጽ ህግ)) ፤ እንዲሁም *Australian Citizenship Act 2007* (the Citizenship Act) (*የአውስትራሊያ ዜግነት አንቀጽ ህግ 2007* (የዜግነት አንቀጽ ህግ)) እንደሆነ ነው።

## የግላዊ ማንነት መለያ

በማይግሬሽንና ዜግነት አንቀጽ ህግ ውስጥ ስለ መረጃ መሰብሰብ፤ መጠቀምና ወይም አውጥቶ ለሌላ አካል መስጠት ማለት እንደ ባዮመትሪክስ (እንዲሁም 'ግላዊ ማንነትዎን መለያ ተብሎ በሚታወቅ' መረጃ ግልጽ የሆነ ማብራሪያ ይሰጣል።)

ስለ ግላዊ መለያዎች በአንቀጽ ህጉ ገለጻ የሚያካተት:

- የጣት አሸራ ወይም የእጅ አሸራ
- የፊትና ትክሻዎች ገጽታ
- በድምጽ ወይም ቪዲዮ የሚታይ ቀረጻ (ለማይግሪሽን አንቀጽ ህግ ጉዳይ ብቻ እና ውሱን አንዳንድ ነገርን የማያካትተ)
- ቁመትንና ክብደትን መለካት
- የዓይን ገጽታ ስማጣሪያ/iris scan
- የግለሰብ ፊርማ፣ ወይም
- በህጉ ውስጥ በተገለጸው መሰረት ሌላ ማንኛውም መለያ።

የባዮመትሪክ/Biometric አሸራ መረጃን (ግላዊ የማንነት መለያ) ከግለሰቦች በመውሰድ ወይም በመውሰድ ማወቅ ይቻል ይሆናል።

- ጉዞ ሸሚካሄድበት ጊዜ ከኤርፖርቲ
- በአገር ውስጥ ሆነው ቪዛ ለሚያመለክቱ (የመከላከያን ቪዛ በሚመለከት)
- በአውስትራሊያ ማህበረሰብ ውስጥ ሆነው ዜግነት ለሌላቸው
- በኢሚግሬሽን እስር ቤት ማቆያ ላሉ
- ለአውስትራሊያ ዜግነት ላመለከቱ ሰዎች ይሆናል።

## የመምሪያ ቢሮ ምን እንደሚያደርግና እኛን ለማነጋገር ዝርዝር መግለጫ

የመምሪያው ተልእኮ ዋና ዓላማ የአውስትራሊያን ደንበር ለመከላከልና በአካባቢው ለሚካሄድ የሰዎችና የእቃዎች እንቅስቃሴን ለመቆጣጠር፤ ይህም ከዚህ በታች ላሉት አስተዋጽኦ እንደተደረገ ለማረጋገጥ ይሆናል:

- ማይግሬሽን/ስደተኛን በመቆጣጠር የወደፊት የአውስትራሊያን መጠበቅ
- የስደተኛ ደህንነት መጠበቅና በዓለም አቀፍ ሰብአዊነት ፖሊሲ ያለውን አስተዋጽኦ ማድረግ
- የደንበር ጥበቃን ለመቆጣጠርና የጉዞ እድል በማግኘት የአውስትራሊያን ድህንነት መጠበቅ
- የወደብ መስተንግዶ አቅርቦትና የንግድ ስታስቲክስ ጥሬ መረጃን ማሰባሰብ
- ህጋዊ የሆነ ንግድ ሥራ እንዲካሄድ ማድረግ
- የአውስትራሊያ ማሪታይም/maritime ደህንነትና የንግድ ፍላጐቶች
- በኣውስትራሊያ ኢሚግሬሽን ህግ መከተልና በሚሰጥ ውሳኔ ላይ ተቀብሎ መከተል
- የአውስትራሊያ ዜግነት ህጎችን ማስተዳደር ነው።

ለማነጋገር ሙሉ አድራሻ በመምሪያው ድረገጽ **www.homeaffairs.gov.au** ላይ ማግኘት ይቻላል።

የርስዎን መረጃ አላግባብ በስህተት ወስደናል ወይም ተይዟል ብለው ካመኑ ማድረግ የሚችሉት:

- በድረገጽ፡ **www.homeaffairs.gov.au/feedback** መስመር ላይ የአስተያየት መስጫ ቅጽን መሙላት
- ለሚከተለው መጻፍ:
  The Manager
  Global Feedback Unit
  GPO Box 241
  Melbourne VIC 3001
  Australia

## መምሪያው የርስዎን ግላዊ መረጃ ከማን እንደሚሰበስብ

በአጠቃላይ መምሪያው (ወይም ኮንትራት በወሰደ አገልግሎት አቅራቢዎች) የርስዎን ግላዊ መረጃ በቀጥታ ከርስዎ፤ እርስዎን ወክሎ ለሚንቀሳቀስ ሥልጣን ለሰጡት ሶስተኛ አካል ወይም በማይግሬሽን አንቀጽ ህግ መሰረት ስልጣ ን አሰጣጥ ዘዴዎች ባካተተ ስማርትጌት/SmartGate እና ሌላ በአውቶማቲክ የድንበር ማጣሪያ ዘዴ የርስዎ ግላዊ መረጃ ይወስዳል። እንዲሁም የርስዎን ግላዊ መረጃ ከሶስተኛ አካል መውሰድ እንችል ሲሆን በዚህ ሊካተት የሚችል ሌላ የአውስትራሊያ መንግሥት ድርጅቶች፣ ህግ አስከባሪ ድርጅቶች፣ የውጭ መንግሥታት፣ ስፖንሰር ደጋፊዎች፣ የህክምና ባለሙያዎች፣ እርስዎ የመረጡት ድርጅቶች፣ ትምህርት አቅራቢዎች፣ ቀጣሪዎች እና ህዝባዊ አባላት መረጃ ለመስተጥ ሲሉ ለመምሪያ ቢሮው የሚያነጋግሩ ናቸው (ለምሳሌ፡ 'ለጥቆማ የስልክ ጥሪዎች') ።

### የኢሚግሪሽንን አገልግሎቶች የሚያካሂዱ ድርጅቶች ወይም ኮንትራክተሮች

ለአንዳንድ የመምሪያ ሥራን ለማካሄድ ሲባል እኛን ወክሎ በሌላ ሥልጣን ያላቸው መንግሥታዊ ድርጅቶች በኩል አንዳንድ ግላዊ መረጃ መሰብሰብና መጠቀም ይችላሉ።

እንዲሁም እኛን በሚወክሉ ኮንትራክተሮች ግላዊ መረጃ መሰብሰብና መጠቀም ይችላሉ። ለምሳሌ፡ በሁለቱም ማለት የሚወጣና የሚገባ የበረራ አየር መንገድ የቅድሚያ ተሳፋሪዎች አሰራር፣ ኮምፑውተር ዘይቤ፣ የጥናት ፍተሻ/ቃለመጠይቅ፣ ለኢሚግሪሽን እስረኞችና ለህክምና አገልግሎቶች የድጋፍ አገልግሎቶች ያካተተ

የመምሪያው ኮንትራክተራክተሮች በአቅስትራሊያ ወይም በውጭ አገር ቢሆኑም በሚስጥራዊ ጥበቃ አንቀጽ ህግ መሰረት ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ አለባቸ ው።

© COMMONWEALTH OF AUSTRALIA, 2020

# በህግ ፍቃድ ማግኘት ለሚያስፈልገው የርስዎን ግላዊ መረጃ መሰብሰብ

የማይግሪሽን አንቀጽ ህግ፣ የ IGOC አንቀጽ ህግ፤ የጉምሩክ ቀረጥ አንቀጽ ህግ፤ ከሃገር የመውጫ አንቀጽ ህግ፣ የማሪታይም ስልጣን አንቀጽ ህግ፤ የዜግነት አንቀጽ ህግ እና የግላዊነት አንቀጽ ህግ እንደሚፈቅደውና በአንዳንድ እንደሚያስፈልገው አንቀጽ ህጉን ለማስፈጸም ሲባል መምሪያው አንዳንድ ግላዊ መረጃ ይሰበስባል።

## የማይግሬሽን አንቀጽ ህግ

ቪዛን ከማመልከት ጋር በተዛመደ መምሪያው:

- ለማመልከቻው ጠቃሚ የሆነ ማንኛውም መረጃ ለመሰብሰብ ሥልጣን አለው (በማይግሬሽን አንቀጽ ህግ ክፍል 56 ይመልከቱ), እንዲሁም
- ግለሰብን የሚገልጽ መለያ እንዲሰጡ ሊጠይቅዎት ይችላል (በማይግሬሽን አንቀጽ ህግ ክፍል 40 እና 46 ይመልከቱ)።

ቪዛ አመልካቾች እና አንዳንድ ቪዛ ያላቸው በሁኔታቸው ላይ ለውጥ ካለ ወይም የማመልከቻ ቅጹን ሲያስገቡ ስህተት መረጃ ካለው ለመምሪያው መናገር አለባቸው (በማይግሬሽን አንቀጽ ህግ ክፍል 104 እና 105 ማየት)።

የማይግሬሽን አንቀጽ ህግና የማይግሬሽን ደንብ ህጎች 1994 ዓ.ም ጉዳይን በሚመለከት አንድ ወይም ከዚህ በላይ የግላዊ ማንነት መለያ ሰነድ ለመምሪያው ቢሮ ማቅረብ ይኖርብዎ ይሆናል።

አውስትራሊያ ሲገቡ የመምሪያ ቢሮ አንዳንድ ግላዊ መረጃ እንዲያቀርቡ ይጠይቃል (ለምሳሌ፡ ለዜጎች ፓስፖርት እና የማንነት መለያ እንዲሁም ለቪዛ ማረጋገጫ ማስረጃ)። ዜግነት ከሌለዎት ታዲያ ለዚህ ጥያቄ የሚሆን ማስረጃ ካልተሰጥዎት ወደ አውስትራሊያ እንዳይገቡ ይደረጋል (በማይግሬሽን አንቀጽ ህፍ ክፍል 257A ማየት)።

ከአውስትራሊያ ሲሄዱ የመምሪያ ቢሮ ከርስዎ አንዳንድ ግላዊ መረጃ እንዲያቀርቡ ሊጠይቅ ይችላል (በማይግሬሽን አንቀጽ ህግ ክፍል 257A ይመልከቱ)።

ህጋዊ ላልሆነ ዜግነት ለሌው ለመለየት የመምሪያ ቢሮ ሊጠይቀው የሚችል:

- የማንነት ማስረጃ መታወቂያ እና የቪዛ ሁኔታ ይህም የግላዊነት መለያን ያካተተ (በማይግሬሽን አንቀጽ ህግ ክፍል 188 ይመልከቱ)።
- ስለ ማንነት ማስረጃ ወይም ተጠርጣሪ ህጋዊ ያልሆነና ዜጋ ያልሆነ የት እንዳለ ሰነዶች ወይም መረጃ ላቀረበ ሰው (በማይግሬሽን አንቀጽ ህግ ክፍል 18 ይመልከቱ)።

በኢሚግሬሽን ቁጥጥር እስር ቤት ላለ ሰው የማንነት መለያ ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት (በማይግሬሽንና የማይግሬሽን ደንቦች ህግ 3.30 ክፍሎች 258 እና 261AA(1) ማየት)።

ከንግድ ሥራ ደጋፊዎች ጋር በተመለከተ መምሪያውና ተገቢ የሆነው Work Ombudsman (FWO) (በሥራ ላይ እንባ ጠባቂ (FWO)) ግላዊ መረጃን ሊሰበስብ የሚችለው ከተቆጣጣሪው በተሰጠ ሥልጣን መሰረት  ሲሆን በማይግሪሽን አንቀጽ ህግ ክፍል/Part 2 በንኡስ ክፍል F ክፍል/Division 3A መሰረት ይሆናል።

በማይግሬሽን አንቀጽ ህግ ክፍል 252  ውስጥ ባለው ምርመራ የማካሄድ ሥልጣን መሰረት በግለሰቡ የቀረበን ሰነድ ወይም በግለሰቡ ቁጥጥር ላይ ያለን በንብረቱ የሚገኙ ሌሎች ነግሮችን ፍቀድ ባለው ህላፊ ተይዞ መቆየት የሚቻል መሆኑ፤ ለምሳሌ፡ ይህ ለግለሰቡ ቪዛ መሰረዝ ማስረጃ ሊሆን ይችላል።

የውሸት ማስመሰያ ሰነድን ህላፊው ማስቀም ማለት መወገድ ይችላል (እንዴት ሰነዱ መወሰድ እንዳለበት በክፍል 487ZJ እና Division 1 of Part 9 የማይግሬሽን አንቀጽ ህግ ማየት)።

## የዜግነት አንቀጽ ህግ

መምሪያው ለግለሰቡ ዜግነት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት እርካታ ለማግኘት የተለያዩ ግላዊ መረጃዎችን ሊሰበስብ ይችላል።

ከዜግነት ማመልከቻዎች ጋር በተዛመደ ግላዊ መረጃዎችን መጠየቀ ይፈቀድለታል ታዲያ ውሳኔ ሰጪው አካል በማንነት መለያ መረጃ ደስተኛ ካልሆነ ማመልከቻውን ላያጸድቅ ይችላል (በዜግነት አንቀጽ ህግ ክፍል/ Part 2 በክፍል/Division 5 እና በክፍል/sections 17(3), 19D(4), 24(3), እና 30(3) ያለውን ማየት)።

የውሸት ማስመሰያ ሰነድን ህላፊው ማስቀም ማለት መወገድ ይችላል (እንዴት ሰነዱ መወሰድ እንዳለበት በክፍል 45B, እና Division 1 of part 3 የዜግነት አንቀጽ ህግ የሚለውን ማየት)።

## የ IGOC አንቀጽ ህግ

በ *Immigration (Guardianship of Children) Act 1946* (the IGOC Act) (*ኢሚግሬሽን (ልህጻናት እንክብካቤ መጉዚት) አንቀጽ ህግ 1946* (የ IGOC አንቀጽ ህግ)) እንዲሁም በህገ ደንቦቹ መሰረት፤ እድሜያቸው 21 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ (እንደ IGOC አናሳ ይባላሉ)። ለአንዳንድ ዜግነት የሌላቸው ወደ አውስትራሊያ የሆነ ሰው አብሮ ከሌለ በኢሚግሬሽን ሚኒስተር የእንክብካቤ አቅርቦት ማድረግ አለበት።

በእንክብካቤ አቅራቢነት ህላፊነት ስለሚካሄድ ስብሰባ የሚረዳ የ IGOC አንቀጽ ህግ ታዲያ ሚኒስተሩ በኮመንዌልዝ ወይም በአስተዳደር ግዛት ወይም ተሪቶርይ መንግሥታት በራሳቸው እንክብካቤ የመስጠት ስልጣን ባለው ተወካይ/ተወካዮች እንዲሰጥ ህጉ ይፈቅድላቸዋል (’ተወካይ እንክብካቤ ሰጪ‘ በሚል ይጠራል)። እንዲሁም በጉዳዩ ላይ ፈቃደኛ ለሆነና ለተስማሙ ሰዎች ወይም ድርጅቶች ለነዚያ IGOC ለአናሳ ‘እንክብካቤ ሰጪ’ ለመሆን መመረጥ ይችላል። በነሱ ቁጥጥር ስር ላለ ህጻን በየቀኑ እንክብካቤ የመስጠት ውሳኔ ለማካሄድ በአጠቃላይ የእንክብካቤ አቅራቢው ምብትና ህላፊነት እንዳለው

በ IGOC አንቀጽ ህግ ስር ላሉ ህጻናት በየቀኑ ለሚካሄድ እንክብካቤና ደህንነት ለማረጋገጥ የመምሪያው ቢሮ ስለ IGOC አናሳ እና ለነሱ እንክብካቤ አሰጣጥ ግላዊ የሆነ መረጃን ለማሰባሰብ ይችላል። በየቀኑ ለሚካሄድ እንክብካቤና ደህንነት ለማረጋገጥ የ IGOC አናሳ በግላዊነት አንቀጽ ህግ መሰረት አስፈላጊ ከሆነ መሟላት አለበት። የመምሪያው ቢሮ ከዚህ በታች ባለው ግላዊ መረዳእታ መስጠትና ለመውሰድ ይችላል:

- የአስተዳደር ግዛት/ተሪቶርይ ባለሥልጣኖች፣ የህጻን ደህንነትን ያካተተ
- የህጻን እንክብካቤ ሰጪ ተወካዮች
- እንክብካቤ ሰጪዎች
- ወላጅ፣ እንክብካቤ ሰጪዎችና ወይም ዘመዳሞችና ወይም
- ሌሎች የአውስትራሊያ መንግሥታዊ ድርጅቶች።

## የጉምሩክ አንቀጽ ህግና ከአገር የመውጫ አንቀጽ ህግ

በጉምሩክ ስርዓት የሚወጣ አንቀጽ ህግ አስተዳደር ስላለ የተለያዩ ግላዊና የንግድ መረጃዎችና ሌሎች ከአውስትራሊያ ህጎች ጋር የተዛመደ (የማይግሬሽንና የግብር ህጎችን ያካተተ) የመምሪያው ቢሮ ለመውሰድ ሥልጣን አለው። በተለይ መምሪያው እነዚህን መረጃዎች የሚወሰድበት ምክንያት የአውስትራሊያን ደንበር ለመከላከልና በደንበሩ ላይ ስለሚካሄድ ጥያቄዎች ለማረጋገጥ ነው።

በጉምርክና በአገር መውጫ አንቀጽ ህጎችና በግብር ህጎች ላይ በተጠቀሰ ጉዳዮች ለርስዎ ግላዊ መረጃ ለመውሰድ ያለንን ቅጽ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ለየት ያለ የማሰባሰቢያ ማሳሰቢያ ሊኖር ይችላል። እንዲሁም በነዚህ ቅጾች ተደርጎ ለየት ያለ መረጃ ማለት እንዴት መረጃ ስለሚወሰድ፤ ስለመጠቀምና በሰነዱ ላይ ያለን ግላዊ የሆነ መረጃ ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠትና በዚህ ላይ ያለን ግላዊ ማሳሰቢያ መነበብ እንዳለበት ነው።

ለምሳሌ፤ በጉምሩክ አንቀጽ ህግ ክፍል 64ACA እና ክፍል 64ACB ላይ በተጠቀሰው መሰረት ወደ አውስትራሊያ ስለሚጓዙትና በመርከብና በአየር ለመጡ ሰዎች የመምሪያው ቢሮ ለጉምሩክ አንቀጽ ህግ፣ ማይግሬሽን አንቀጽ ህግና ሌላ ህጎች ስለሚጠቅም አንዳንድ ግላዊ የሆኑ መረጃዎችን መውሰድ ያስፈልጋል።

## የማሪታይም/Maritime ሥልጣን አንቀጽ ህግ

በውሃ ላይ ያለን ደንብ አስገዳጅ ድርጅቶች ያለን እንቅስቃሴየማሪታይም ሥልጣን መሰረት የመምሪያው ቢሮ ግላዊ የሆኑ መረጃዎችን ለመውሰድ ይፈቀድለታል። ይህ የሥልጣን ሀይል ከአውስትራሊያ ማሪታይም ጋር በተዛመደ ህጎች ማለት ህጋዊ ያልሆነ በውጭ አገር አሳ ማጥመድ፤ ጉምሩክ፣ ማሪታይም የህውከት ፈጠራ መቆጣጠሪያና ህጋዊ ያልሆነ የአደገኛ እጽ እንቅስቃሴ እንዲሁም በባህር ክልል ለዓለም አቀፍ ስምምነትና ዝግጅት የሚያስገድድ ሥልጣን አለው።

## ግላዊነት አንቀጽ ህግ

የግላዊነት አንቀጽ ህግ ለመሰብሰብ የሚፈቅደው:

- በህግ ከተፈቀደ በጣም ዘግናኝ  የሆኑ መረጃዎችን፣ ወይም ከህግ ግዳጅ ጋር የተዛመዱ ሥራዎችን፣ ወይም እርስዎ ፈቃድ ከሰጡ ይሆናል
- አስፈላጊ ከሆነ ሌላ ግላዊ መረጃን፣ ወይም በቀጥታ ግንኙነት ያለውን፣ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የመምሪያውን ሥራ ወይም እንቅስቃሴዎች ይሆናል።


© COMMONWEALTH OF AUSTRALIA, 2020

### መምሪያው በድርጅቱ ህግ ማስገደጃ መሰረት ተግባራዊ ያደርጋል

በሚቀጥለው አንቀጽ ህጎች መሰረት የ the *Crimes Act 1914*, the *Criminal Code Act 1995*, the *Australian Nuclear Science and Technology Organisation Act 1987* (the ANSTO Act) and the *Independent National Security Legislation Monitor Act 2010 (የወንጀል አንቀጽ ህግ 1914፣ በወንጀል ትግባር አንቀጽ ህግ 1995፣ የአውስትራሊያ ኑኩሊያር ሳይንስና ተክኖሎጂ ድርጅት አንቀጽ ሕግ 1987* (the ANSTO Act) *እንዲሁም ተጽዕኖ በሌለበት የአገር አቀፍ ደህንነት ህጎች ቁጥጥር አንቀጽ ህግ 2010)* መሰረት የህግ ማስገደጃ ድርጅት እንደሆነና ታዲያ ይህን ሥራ ለማካሄድ በነዚህ አንቀጽ ህግ ግላዊ የሆነን መረጃ ማሰባሰብ ይችላል።

## የርስዎን ግላዊ መረጃ የምንሰበስብበት ምክንያት

ግላዊ የሆነ መረጃን የምንሰበስብበት ዋናው ዓላማ ባለዎት የኢሚግሬሽን ጉዳይ እና/ወይም ወደ ዜግነት መሸጋገሪያ መንገድ እና በደንበር ላይ የእቃዎች እንቅስቃሴ በተዛመደ የመምሪያውን ተግባርና ሥራ ለማከናወን ነው። ከዚህ የሚከተሉትን መርሃግብሮች እንቆጣጠራለን:

- ቪዛ እና ማይግሬሽን/መጤ
- ሰደተኛ እና በሰብአዊ ርህርሄ እርዳት ለመስጠት በጉምሩክና ከአገር ማስወጫ የሚካተት አንዳንድ ሌሎች የአውስትራሊያ ህጎች ማለት ለግብር ቀረጥ፣ ጤና ጥበቃና፣ የንግዲ ሥራ፣ ወንጀል፣ ለመማር ንብረት እና ለማህበረሰብ መከላከያ ያጠቃለለ ይሆናል።
- ሰደተኛ እና በሰብአዊ ርህርሄ እርዳት ለመስጠት
- ደንበርን መቆጣጠር
- ለቪዛ የሚያሟላ እና ለኢሚግሬሽን ጉዳይ መፍትሄ ማስገኘት
- ለኢሚግሬሽን እስር ቤት፣ ማስወገድ ወይም ወደ ክልላዊ የአሰራር ሂደት ማእከል ማስተላለፍ (በዚህ የሚካተቱት አገልግሎት አቅራቢዎች እና ከአገር ውጭ ሆኖ የአሰራር ሂደት ለሚያካሂዱ የሚረዱ የውጭ አገር ያሉ ባለሥልጣኖች ሲሆኑ ይህም እንደ ህግን ማስከበር፣ ለሰፈራና በጎ አድራጎት አገልግሎቶችን ማቅረብ)
- ለዜግነት።

በቪዛ፣ በድጋፍ መስጫ፤ ንግድ፣ እቃ ከአገር ማስወጣትና ማስገባት፣ ኳራንቲን ማጣሪያ ወይም ወይም በዜግነት ማመልከቻ ላይ የሚሰጡት መረጃ የሚጠቅመው መሰረታዊ ለሆነ ጉዳይ ይሆናል።

በግላዊነት አንቀጽ ህግ መሰረት የሚሰጡት መረጃ በጣም አስፈላጊ ላልሆነ ጉዳይ ሊጠቅም ይችላል። በአጠቃላይ መምሪያው የርስዎን መረጃ የሚጠቀመው ወይም አሳልፎ የሚሰጠው በዚህ መልጉ ስለመሆኑ ግምት ውስጥ ያስገቡት። እንዲሁም በሁለተኛ ደረጃ አስፈላጊ ላልሆነ ጉዳይ በቀጥታ ከመሰረታዊ ጉዳይ ጋር ይዛመዳል (በጣም ዘግናኝ ለሆነ መረጃ) ወይም ከመሰረታዊ ጉዳይ ጋር የተዛመደ (ለሌላ ግላዊ መረጃ)። ለምሳሌ፡ በቪዛ ማመልከቻው ላይ ያቀረቡት መረጃ ምናልባት በተከታታይ ካቀረቡት ማመልከቻዎች ጋር በተዛመደ ሊጠቅም ይችላል፤ *Freedom of Information Act 1982* (በመረጃ ነጻነት ኣንቀጽ ህግ 1982ዓ.ም እና በግላዊ አንቀጽ ህግ ውስጥ የተካተተ)። ከዚህ ባሻገር ስለ ማይግሬሽን ጉዳይ ለማነጋገር በሰጡን አድራሻ አድርገን በኤሌክትሮኒክ ግንኙነት ማድረግ እንችላለን።

## የርስዎ ግላዊ መረጃ በኢሚግሬሽን መምሪያ ካልተወሰደ የሚያስከትለው

የርስዎ ግላዊ መረጃ ካልተወሰደ ታዲያ ላቀረቡት የቪዛ ወይም ዜግነት ወይም (አስፈላጊ ለሆነ) የንግድ ሥራ፣ እቃዎችን ከአገር ውስጥ ማስወጣትና ማስገባት፣ የኳራንቲን ማጣሪያ ለማድረግ ማመልከቻ መምሪያው ሥራውን ማካሄድ እንደማይችል እና ለርስዎ የሚሆን የድጋፍ አገልግሎት አይሰጥም።

የርስዎን መረጃ አለመሰብሰብ ለመምሪያው የተሰጠውን ህጋዊ ግዴታ መወጣትና ማሟላት እንዳልቻለ ሲሆን (በተለይ ከቅሬታ ጋር የተዛመደ) ታዲያ በእንክብካቤ አሰጣት ያለውን ግዴታ ወይም የአውስትራሊያን ዓለም አቀፍ ግዴታን መጣስ ይሆናል።

## የርስዎን ግላዊ መረጃ ለሶስተኛ አካላት መደበኛ ሚስጢር አወጣጥ

### ለተመረጠ ተወካይ ሚስጢር ማውጣት

አንድ ሰው ከመረጡ ማለት እንደ ለቤተሰብ አባል፣ ማይግሬሽን ተወካይ፣ ለጉምሩክ ተቋራጩች፣ ለጉዞ ወይም አየር መንገድ ተወካይ፣ ለአቤቱታ ሰሚ፣ ለፓርላማ አባል፣ ወይም እርስዎን የሚወክል ለህግ ጠበቃ ያለዎት ግላዊ መረጃ ለነዚህ ሶስተኛ አካላት መረጃው እንዳይሰጥ ካልጠየቁ በስተቀር አውጥቶ ሊሰጥ ይችላል።

የርስዎ ግላዊ መረጃ ስፖንሰር ለሚያደርጉለት ወይም ድጋፍ ለሚያደርግልዎት ሰው ሚስጢር ሊወጣ ይችላል።

### ለሌላ መንግሥታዊ ድርጅቶች መደበኛ ሚስጢር አወጣጥ

መምሪያው ያለውን ሥራ ለመቆጣጠር በሚል ዓላማ በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ ግላዊ መረጃ አውጥቶ ለሌላ መንግሥታዊ ድርጅቶች ለመስጠት ሥልጣን ይኖረዋል ወይም በደንበር ጥበቃ ሀይል አንቀጽ ህግ ወይም ህጎች መሰረት ሲፈቀድ ግላዊ የሆነ መረጃን መስጠት አለበት። ለምሳሌ የርስዎን ማንነት ለመለየት፤ ሰነዱን ለሰጠ ባለሥልጣን ለማወቅ ከጥሬ መረጃዎች ጋር በማመዛዘን፣ ወይም የቅሬታ ግዳጅን በመቆጣጠር ያካተተ ይሆናል።

መረጃ ከምንቀያየርበት ውስጥ የሚካተተ መንግሥታዊ ድርጅቶች ሲሆኑ ነገር ግን በሚከተሉት የተወሰኑ አይደሉም:

- የሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ (DHS)፤ የ*Social Security Act 1991* (*የማሕበራዊ ደህንነት አንቀጽ ህግ 1991 ዓ.ም*) ለማስተዳደር የ*Child Support (Assessment) Act 1989* (*የህጻን ድጋፍ (ግምገማ) አንቀሰ ህግ 1989*) እንዲሁም የ *Child Support (Registration and Collection) Act 1988* (*የህጻን ድጋፍ (ምዝገባና መረጃ መሰብሰብ) አንቀድ ህግ 1988*) ለማስተዳደር መተግበር
- የማሕበራዊ አገልግሎት መምሪያ
- የእርሻ መምሪያ ቢሮ ለአውስትራሊያ የተፈጥሮ/ባዮሰኵሪቲ ደህንነት አሰራርሓን ለ *Quarantine Act 1908* (*ኳራንቲን አንቀጽ ህግ 1908*)፣ ለ *Export Control Act 1982* (*ከአገር ውጪ ለሚወጡ እቃዎች ለመቆጣጠር አንቀጽ ህግ 1982*) እንድሁም ለ *Imported Food Control Act 1992* (*ከአገር ውጪ ለሚገቡ እቃዎች ለመቆጣጠር አንቀጽ ህግ 1992*) ማስተዳደር
- ለህክምና/ Therapeutic እቃዎችን መቆጣጠር
- የኢንዱስትሪ፤ ለውጥ እና ሳይንስ መምሪያ
- Australian Sports Anti-Doping Authority (የአውስትራሊያ ስፖርቲ ጸረ-ዶቢንግ ባለሥልጣን) ለ National Anti-Doping Scheme (አገር አቀፍ -ጸረ-ዶቢንግ ሥልጣን)
- የትምህርት መምሪያ የ*Education Services for Overseas Students Act 2000 (ለውጭ አገር ተማሪዎች የትምህርት አገልግሎቶች አንቀጽ ህግ 2000 ዓ.ም)* አገልግሎቶችን ለማስተዳደር
- የሥራ ቀጣሪና ተቀጣሪ፤ ሙያ፤ የመለስተኛ ቤተሰብ ንግድ ሥራ መምሪያ ስለ ሥራና ሰራተኛ አገልግሎቶች ጥሬ መረጃን ለማመዛዘን
- በውትድርና ላገለገሉ ሽማግሌ ጉዳይ መምሪያ የ *Veterans' Entitlements Act 1986 (በውትድርና ላገለገለ ሽማግሌ አንቀጽ ህግ 1986 ዓ.ም)* ለማስተዳደር
- የአውስትራሊያ መገበሪያ ጽህፈት ቤት (ATO), የ *Income Tax Assessment Act 1997* (*የገቢ መጠን ግብር ግምገባ አንቀጽ ህግ 1997 ዓ.ም*) ለላ የቀረጥ ማስገበሪያ ሕጎችን ለማስተዳደር
- ተገቢ የሥራ እንባ ጠባቂ (FWO), ለ *Fair Work Act 2009* (*ተገቢ የሥራ አንቀጽ ህግ 2009*) ተግባራዊ ለማድረግ
- የውጭ ጉዳይና ንግድ መምሪያ (DFAT), የ *Australian Passport Act 2005* (*የአውስትራሊያ ፓስፖርት አንቀጽ ህግ 2005 ዓ.ም*) ለማስተዳደር እና ለመከላከያ ቪዛ አሰራር ሂደት እና ከሁለት አገር ያለው የውጭ አገር ፓስፖርት ለተፈቀደለት የሚጠቅም መረጃ ከመጣበት አገር ለማግኘት
- የአውስትራሊያ መራጮች ኮሚሽን የ *Commonwealth Electoral Act 1918 (የኮመንዌልዝ መራጮች አንቀጽ ህግ 1918 ዓ.ም)* ለማስተዳደር ይሆናል።

### የግምገማ፣ ኦዲትና ማጣሪያ አካላት

በቀረበ ውሳኔ ላይ እንደገና በህጋዊ እንዲታይ ካመለከቱ ታዲያ መምሪያው ጠቃሚ የሆኑ ግላዊ መረጃዎችን ጉዳዩን ለሚያይ ልዩ ፍርድ ቤት ወይም መደበኛ ፍርድ ቤት ይሰጣል።

ከአጣሪ መርማሪ አካላት ጋር በጋራ መረጃ እንጠቀማለን እነዚህም እንደ:

- ኮመንዌልዝ መንግሥት አቤቱታ ሰሚ
- የአውስትራሊያ መረጃ ኮሚሽነር ጽህፈት ቤት
- የአውስትራሊያ ሃገር አቀፍ ኦዲት ማጣሪያ
- የአውስትራሊያ ሰብአዊ መብቶች አስጠባቂ ኮሚሽን
- የተገቢ ሥራ ጉዳይ አቤቱታ ሰሚ።

© COMMONWEALTH OF AUSTRALIA, 2020

### በድንገተኛ ችግርና በህግ ማስገደድ

ምናልባት በድንገተኛ ሁኔታ፣ ከፍተኛ ጉዳት ወይም ሞት በሚከሰትበት ጊዜ ለማነጋገር የርስዎን ግላዊ መረጃ ለአውስትራሊያ ህግ አስከባሪ ድርጅቶች ወይም ለድንገተኛ ችግር አገልግሎት መሰጠት ይኖርበታል።

እንዲሁም በወንጀል ህግ ለማስገደ አስፈላጊ ከሆነ መምሪያው ሚስጢር መረጃን ለአውስትራሊያ (ኮመንዌልዝ፣ አስተዳደር ግዛትና ተሪቶርይ መንግሥት) እና ለውጭ አገር ሰዎች አስገዳጅ ድርጅቶች ወይም አካላት፤ አስፈላጊ ከሆነ ማስገደድን በተዛመደ ሥራዎችን ማለት እንዳይገባ ማድረግ፤ በቁጥጥር እስርቤት ማቆየት፤ በምርመራ ማጣራትና ወንጀል ለፈጸመ ቅጣትን ያካተተ ልህግ አስከባሪዎች ድርጅቶች አስተላልፎ ይሰጣቸዋል።

## ስለ ድጋፍ መርሃግብሮች

በቪዛ አሰራር ሂደት ላይ የተሰበሰበ መረጃ ምናልባት አሳልፎ መስጠት የሚቻል:

- የሰፈራ ድጋፍን ለማካሄድ ለማሕበራዊ አገልግሎቶች መምሪያ
- የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስልጠናን ለማሳለጥና ለመቆጣተር የኢንዱስትሪ፤ ለውጥ እና ሳይንስ መምሪያ ተግባር ይሆናል።

## ለመንጃ ፈቃድ ባለሥልጣናት መረጃ መስጠት

በአውስትራሊያ ውስጥ ለመንጃ ፈቃድ ካመለከቱ ስላለዎት የማይግሬሽን ፈቃድና የመሥራት ፈቃድዎ በተመለከተ እንዲሁም በሆነ መልኩ የአውስትራሊያ ዜግነት ካለዎት በመምሪያው በኩል መረጃ ለሚመለከተው ባለሥልጣን ይሰጣል። ይህ መረጃ የሚጠቀመው የመንጃ ፈቃድ ለመያዝ የርስዎን ብቃት ለማየት ነው። እንድሁም በጉምሩክ አንቀጽ ህግ መሰረት ለሆነ ፈቃድ በምትጠይቅበት ጊዜ መሰጠት ያለበት ለየት ያለ መረጃ ሊኖር ይችላል።

## የግላዊ መረጃ አሳልፎ የመስጠት ህጋዊ ፈቃድ

'የግላዊ ማንነት መለያ' በገጽ 1 ላይ ተገልጿል።

በማይግሪሽን አንቀጽ ህግ ክፍል/ Part 4A እና ክፍል s43 መሰረት መምሪያው በተለያየ ሁኔታ ላይ ለግላዊ ማንነት መለያ አሳልፎ የመስጠት ስልጣን አለው። ለምሳሌ በዚህ የሚካተት:

- ለቪዛ ደረጃ ወይም ለዜግነት ግልጽ ለማድረግ
- የወንጀል ህግን ለማስገደድ
- ከአውስትራሊያ መንግሥት ድርጅት ጋር የተቀናጀ የማንነት መለያ መረጃን ለመቀያየር
- ለመደበኛ ፍርድ ቤት፣ ልዩ ፍርድ ቤት ወይም ለዓለም አቀፍ አካል የሚቀርብ ጠቃሚ መረጃን ማዘጋጀት
- በአውስትራሊያ ህግ መሰረት አስፈላጊ ከሆነ ነው።

እንዲሁም በዜግነት አንቀጽ ህግ መሰረት ለዜግነት ወይም ማይግሬሽን ህግ አሰራር ሲባል መምሪያው የግላዊ ማንነት መለያ መረጃን ለሌላው ይሰጣል።

እንዲሁም በማይግሬሽን አንቀጽ ህግ ክፍል/Part 4A መሰረት መምሪያው በሚከተሉት ሁኔታ ያሉትን ግላዊ መረጃ ለሌላ የመስጠት ስልጣን ይኖረዋል:

- ጥሬ መረጃን ከሚከተሉት ጋር ማመዛዘን:
  - አንድን ሰው መለየት፣ ወይም የአንድን ሰው እውነተኛነት ማጣራት
  - አውስትራሊያ ለሚገቡ ወይም ለሚወጡ ሰዎች የሚቀርብ ሥራ ቅንጅት
  - በባህሪ አሳሳቢ ጉዳይ ወይም በሃገራዊ ደህንነት አሳሳቢ ጉዳይ በሆነ የወንጀል ታሪክ ያለበትን ዜግነት የሌለውን ሰው መለየት
  - በኢሚግሬሽን ጉዳይ ላይ የውጊያ ትግል ሰነድ እና የተጭበረበረ መታወቂያ መለየት
  - በመከላከያ ቪዛ አሰራር ሂደት ላይ መርዳት
- አንድን ሰው ለይቶ ለማውጣት ወይም ያለበትን ማወቅ (በማይግሬሽን አንቀጽ ህግ ክፍል 33FA እና 33FC ያሉትን ማየት)
- የመርማሪ አካላትን ለማሳወቅ ማለት እንደ በአውስትራሊያ የአገር አቀፍ ኦዲት መርማሪ ጽህፈት ቤት እና የአውስትራሊያ ሰብአዊ መብቶች አስከባሪ ኮሚሽን የሚካሄድን ምርመራ ማሳወቅ
- አንድን ሰው ከአውስትራሊያ ለማስወጣት ወይም ወደ አውስትራሊያ ለማስገባት ሲባል ከውጭ አገር መንግሥታት ጋር ቅንጅት ለመፍጠር
- የማይግሬሽንን ጉዳይ ለመቆጣጠር በሚል ዓላማ ለታወቁ የውጭ አገር መንግሥታት፣ የህግ አስከባሪዎች ወይም ለውጭ አገር መንግሥታት ደንበር ተቆጣጣሪ አካላት ወይም ለታወቁ የዓልም አቀፍ ድርጅቶች መረጃ ለማቀናጀት ይሆናል (በማይግሬሽን አንቀጽ ህግ ክፍል 5A(3) ማየት)
- በዓለም አቀፍ ወንጀል ነክ ጉዳዮች ላይ እርዳታን ለማግኘት ወይም ለመስጠት ይሆናል።

ስለ ግላዊ ማንነት መለያ የበለጠ መረጃ ለማግኘት የቅጽ 1243i ይመልከቱ።

የሰራተኛን ቪዛ በተመለከተ መምሪያው ስለ ደጋፊ ስፖንሰር ወይም ቪዛ ለያዘው ሰው ያለውን መረጃ ከአንዳንድ ግላዊ መረጃ ጋር ለማመሰካከር ሲባል መረጃን ለሌላ አሳልፎ ይሰጣል (በማይግሬሽን አንቀጽ ህግ ክፍል 140ZH እና ደንቦች ቁጥር 2.103, 2.104 እና 2.105 ማየት)።

እንዲሁም በደንበር ማስገደጃ ሥልጣን አንቀጽ ህግ ክፍል/Part 6 መሰረት በተወሰኑ ሁኔታዎች ላይ ላሉ ግላዊ የሆኑና በኢሚግሬሽንና ደንበር ጠባቂ የተያዘን መረጃ (ክፍል 4(1) የደንበር ማስገደጃን ማየት) ለሌላ አካል አውጥቶ የመስጠት ሥልጣን እንደተሰጠው ነው። በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ የደንበር ማስገደጃ ሥልጣን አንቀጽ ህግ ከዚህ በታች ባሉ አካላት የግላዊ የሆነን መረጃ ማግኘት ይፈቀድላቸዋል:

- ለኮመንዌልዝ፣ ለአስተዳደር ግዛቶችና ተሪቶርይ ድርጅቶች ወይም ባለስልጣኖች
- ለአውስትራሊያ ፈደራል ፖሊስ (AFP) ወይም ለአስተዳደር ግዛቶች ወይም ተሪቶርይ አገልግሎት
- ለሬሳ ማጣሪያ መርማሪ አካል
- ለኮመንዌልዝ፣ ለአስተዳደር ግዛቶች ወይም ተሪቶርይ ህጋውነት ላላቸው ቢሮዎች (ለምሳሌ፡ እንባ ጠባቂ/Ombudsman)
- በአውስትራሊያ ደንበር ጥበቃ ሀይል (Secrecy and Disclosure) (ሚስጥራዊ የሆነን አሳልፎ መስጠት) ደንብ ህግ/Rule 2015,¬ ማለት የአውስትራሊያ ቀይ መስቀል ማህበረሰብ ለመሳሰሉ አካላት ወይም ሰዎች
- ለውጭ አገር ወይም ህዝባዊ የዓለም አቀፍ ድርጅት።

ይህም ሆኖ በደንበር ጥበቃ ማስገደጃ ሥልጣን አንቀጽ ህግ ክፍል/Part 6 መሰረት ለሚያስፈልግ ለየት ያለ ቅድመ ሁኔታ በተጨማሪ በደንበር ጥበቃ ማስገደጃ ስልጣን ኣንቀጽ ህግ ክፍል/Part 6 መሰረት በወጣው የግላዊ መረጃ አሰጣጥ ፈቃድ ከዚህ በላይ ካሉት አካላት አንደኛው ብቻ መስጠት ይሆናል። ለምሳሌ፡ ከዝህ በታች ካሉት የአንደኛውን ዓላማ ያካተተ:

- የአስተዳደር ወይም ለወንጀል ህግ ማስገደጃ ወይም ከንግድ ሥራ ጋር በተዛመደ ህግ
- ለአስከሬን ሞት ጥያቄ ማጣሪያ ምርመራ ወይም ለቀረበ ጥያቄ የሚረዳ
- ለህዝባዊ ጤና ጥበቃ መከላከያ፤ ወይም ለአንድ ሰው ወይም ከአንድ ሰው በላይ ህይወት ወይም ደህንነት ለመከላከል
- በ *Census and Statistics Act 1905* (*ህዝብ ቆጠራና ስታቲስቲክስ አንቀጽ ህግ 1905*) ወይም በ *Australian Bureau of Statistics Act 1975* (*አውስትራሊያ ቢሮ ኦፍ ስታቲስቲክስ አንቀጽ ህግ 1975*) መሰረት የመረጃ ስዝታቲስቲክስ ማሰባሰብና ግልጽ ማድረግ
- ለህዝባዊ ሁብት ለመከላከል
- የአንድ ሰው ማንነትን ወይም ዜግነት ወይም ያለውን የቪዛ ሁኔታ ለመለየት
- የአውስትራሊያ ዜግነት ለሌላቸው ሰዎች አገልግሎቶችን ለማቅረብ
- የአገር አቀፍ ጸረ-መቀራረብ አሰራርን ለመቆጣጠር
- ከኢሚግሬሽን፣ ከኳራንቲን ጋር በተዛመደ ወይም በአውስትራሊያና በውጭ አገር መካከል ያለን ደንበር ለመቆጣጠር
- በተለያዩ ህጎች ላይ የተካተተን ማለት በ *Customs Act, Migration Act, Maritime Powers Act, Citizenship Act, IGOC Act,* (ጉምሩክ አንቀጽ ህግ፤ በዜግነት አንቀጽ ህግ፤ በ IGOC አንቀጽ ህግ፤ ወዘተ.) ጉዳዮችን ላካተቱ
- ከጦር መከላከያ ሀይል ወይም ከአገር አቀፍ ደህንነት ጋር የተዛመደ ጉዳይ ይሆናል።

እንዲሁም ግላዊ የሆነን መረጃ ለመጠበቅ ያቀረበው ግለሰብ እንዲወጣ ፈቃድ ከሰጠ ታዲያ መምሪያው መረጃን ለሌላ አካል አሳልፎ መስጠት የሚቻለው ይህንን መረጃ በመስጠት ግለሰቡን ለመከላከል ወይም በዚህ ሥልጣን አማካኝነት ለህይወት አስጊ የሆነን ችግር ለመቀነስ ወይም የግለሰቡን ጤና ለመከላከል ጠቃሚ ከሆነ ወይም መረጃው ህጋዊነት ባለው መልኩ ለህዝባዊ አገልግሎት ቀደም ብሎ ተሰጥቶ ከሆነ ነው።

በአንቀጽ ህጉ ክፍል/ Part 6 አንዳንድ ፈቃድ ሓደሓደ ፍቓድ መሰረት ለደንበር ማስገደጃ ሥልጣን አንቀጽ ህግ ክፍል/ Section 51 በመውሰድ ለግላዊ የሆነ አንቀጽ ህግ ጉዳይ በተመለከተ መረጃን በማውጣት ለሌላ አካል መስጠት ይፈቀድልዎታል።

በተጨማሪ ደግሞ መምሪያው ለሰራተኛ መቆጣጠር ወይም አገልግሎት ለመስጠት ከሆነ በደንበር ጥበቃ ማስገደጃ ስልጣን አንቀጽ ህግ መሰረት በኢሚግሬሽንና ደንበር ጥበቃ ያለውን መረጃ አውጥቶ ለመስጠት ይፈቀድልዎታል። እንደዚህ ዓይነት ግላዊ የሆነ መረጃ በሚወጣበት ጊዜ በግላዊ አንቀጽ ህግ መሰረት እንደሚሆን መምሪያው ማረጋገጥ አለበት።


© COMMONWEALTH OF AUSTRALIA, 2020

እንዲሁም በተወሰኑ ሁኔታዎች ከጉምሩክ ህጎች ጋር በተዛመደ ደንቦች ለተቀመጠ ግላዊ መረጃ መምሪያው ለሌላ አካል አሳልፎ የመስጠት ስልጣን አለው።

## ቦታ ሲቀይሩ ላይ ያለን ምዝገባ ማውጣት

ተጓዦች ከአውስትራሊያ ሲወጡና ሲገቡ የገባና የወጣ ምዝገባ ተጓዥ በእንቅስቃሴ ማድረጊያ ጥሬ መረጃ ይያዛል። ምናልባት ለሚከተለው ጉዳይ ሲባል ሊወጡ ይችላሉ:

- የማይግሬሽን አንቀጽ ህግ
- የ *Family Law Act 1975* (የቤተሰብ ህግ አንቀጽ ህግ 1975 ዓ.ም)
- የጉምሩክ ወይም የቀረጥ ህጎች
- ተገልሎ የሚቀይበት ወይም የጤና ህጎች
- ህግ አስከባሪ
- የ *Education Services for Overseas Students Act 2000* (ለውጭ አገር ተማሪዎች የትምህርት አገልግሎቶች አንቀጽ ህግ 2000 ዓ.ም)
- በኮመንዌልዝ፣ አስተዳደር ግዛት ወይም ተሪቶሪ ህግ አወጣት የተገለጸ እንደ ለመጀመሪያ የቤት ባለንብረት ለሆነ መርሃግብር ማስተዳደር ወይም የህጻናት እና/ወይም የበጎ አድራጎት መርሃግብሮችን መቆጣጠር።

## ለህጋዊ ግዳጅና ከዚህ ጋር በተዛመደ ጉዳይ መረጃን ማውጣት

በማይግሬሽን እና ዜግነት አንቀጽ ህጎች መሰረት ለህግ ማስገደጃ ተግባራት ከህጋዊ ግዳጅና ከዚህ ጋር በተዛመደ ጉዳይ (በማይግሬሽን/መጤ እና ዜግነት አንቀጽ ህግ እና ማስገደጃ ተግባራት በሌላ የማስገደጃ አካላት መሰረት የማስገደጃ ተግባራትን ያካተተ) ለህጋዊ ማስገደጃና በተዛመደ ጉዳይ ላይ በመምሪያው በኩል መረጃዎችን አሳልፎ የመስጠት የተለመደ ሲሆን በዚህ የሚካተት:

- በአውስትራሊያና የውጭ አገር ህግ አስከባሪ ድርጅቶች ለሚፈለግ ገጸ-ባህሪ ለማጥናትና ለማስገደድ
- በአውስትራሊያና የውጭ አገር ህግ አስከባሪ ድርጅቶች እና መረጃ ሰብሳቢ ድርጅቶች ወይም ኮሚሽኖች፣ የአገር አቀፍ መደበኛ ፖሊስ አገልግሎት፣ አቀፍ አለም አቀፍ ፖሊስ፣ የአገር ደንበር አነጣጣሪ ማእከል፣ ወንጀል እገታ/CrimTrac፤ AusTRAC፤ ተቆጣጣሪ ኮሚሽኖች፣ ለጥያቄ የፓሪያመንት ኮሚሽኖች፣ አለም አቀፍ ልዩ ፍርድ ቤቶች እና የውጭ አገር ኢሚግሬሽን ባለሥልጣኖች በኢሚግሬሽን የሚደረገውን ማጭበርበር፣ የሃገር አቀፍ ደህንነት ጉዳዮች ለይቶ ለማወቅ ወይም ለማጣራት ወይም በጦር ወንጀር ላይ በጸረ ሰብአዊ ድርጊት ወንጀል ተሳትፎ ጥርጣሬ ላላቸው ሰዎች ለይቶ ለማወቅና ለማጣራት ይሆናል
- የአውስትራሊያ ኮሚሽን ህግ አስገዳጅ ከ *Law Enforcement Integrity Commissioner Act 2006* (ህግ ማስገደጃ ህባራዊ ኮሚሽነር አንቀጽ ህግ 2006 ዓ.ም) ጋር በጋራ ሆኖ ለማስተዳደር
- ሰዎች ከሥራ ቪዛ ሁኔታ በተዛመደ ያላቸውን ህግን ከጣሱ ታዲያ የት እንደሚሰሩ ለ ATO, DHS እና ሌላ የኮመንዌልዝ ወይም የአስተዳደር ግዛትና ተሪቶርይ ድርጅቶች ለመጠቆም
- ህጋዊነት የሌላቸው ዜጎች እንዳሉ ለ AFP እና ለአውስትራሊያ ፖሊስ ሰራዊት ለመጠቆም
- በህዝባዊ የወንጀል ከሳሽ ዳሬክተር ለማይግሬሽን ወይም ዜግነት ጽህፈት ቤት በወንጀል ክስ ያቀርባል
- የውጭ አገር መንግሥታት ህጋዊነት ለሌላቸው ዜጎች ለማስወጣት
- FWO፤ ፈቃድ ያላቸው የትምህርት ተቋማት፣ ቀጣሪዎች፣ ስፖንሰር የተደረጉ፣ ስፖንሰር ድጋፍ ያደረጉ ሰዎች እና ከቪዛ ሁኔታ እና ከስፖንሰር መሆን ግዴታ ጋር በመጠኑ ለሚያሟሉና በድንገት ለሥራ ማገጃ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ህግ ለሚጥሱ ይሆናል።
- ለህግ አስገዳጅ ወኪሎች ማለት ስለ ግላዊ የቪዛ አመልካቾችና ጠያቂዎች በስደተኛና ሰብአዊነት ፕሮግራም መሰረት ለሚቀርብ ጥያቄ ከ AFP (አውስትራሊያ ፌደራል ፖሊስ) ጋር በተዛመደ ማንኛውንም ህጋዊ ግዳጅ ወይም የሃገር አቀፍ ደህንነት ጉዳዮችን ለማጣራት ያካተተ ይሆናል።

## እንደ በህግ አስገዳጅ ድርጅት መጠን መምሪያው መረጃን አውጥቶ ለሌላ መስጠት

በሚቀጥለው አንቀጽ ህጎች መሰረት የ the *Crimes Act 1914*, the *Criminal Code Act 1995*, the *Australian Nuclear Science and Technology Organisation Act 1987* (the ANSTO Act) and the *Independent National Security Legislation Monitor Act 2010* (*የወንጀል አንቀጽ ህግ 1914፣ በወንጀል ትግባር አንቀጽ ህግ 1995፣ የአውስትራሊያ ኑኩሊያር ሳይንስና ተክኖሎጂ ድርጅት አንቀጽ ሕግ 1987* (the ANSTO Act) *እንዲሁም ተጽዕኖ በሌለበት የአገር አቀፍ ደህንነት ህጎች ቁጥጥር አንቀጽ ህግ 2010)* መሰረት ለአንዳንድ ጉዳዮች መምሪያው የህግ ማስገደጃ ድርጅት እንደሆነ ታዲያ በነዚህ አንቀጽ ህጎች መሰረት የራሱን ሥራ ለማስፈጸም ሲል ግላዊ የሆነን መረጃ ለሌላ አካል አውጥቶ ሊሰጥ ይችላል።

## ከመርሃግብር ጋር በተዛመደ ሌላ መረጃ ማውጣት

### ለዋስትና ድጋፍ

ለዋስትና ድጋፍ ከሚሰጡ ሰዎች ጋር በተዛመደ ለማስያዣ የተከፈለን ገንዘብ ለመመለስ ማመቻቸት ወይም የሚከፈል እዳን ማካካሻ ለማጣራት ሲባል ለሴንተርሊንክ መረጃ ይሰጣል።

### ሥራና ሰራተኛ፣ የወዛደር አቅርቦትና የንግድ ሥራ ችሎታ

ስለርስዎ የማይግሬሽን ሁኔታ፣ የሥራ ፈቃድ ስለመኖር እና ለቀጣሪዎች ያለዎት የቪዛ ዓይነትና የጊዜ ገደብ፣ የርስዎን አገልግሎት በሰራተኛ አቅርቦት አስተዳደር በኩል ለሚጠቀሙ የሰራተኛ አቅራቢዎችና ለሶስተኛ አካላት መምሪያው መረጃ አውጥቶ መስጠት ይችላል። ለምሳሌ፡ ለሥራ በሚያመለክቱበት ጊዜ ለመሥራት ስለሚፈቀድልዎ መረጃ ለቀጣሪው ወይም ለሰራተኛ አቅራቢው በመምሪያው በኩል ሊሰጥ ይችላል።

እንዲሁም መምሪያው መረጃ አውጥቶ መስጠት የሚችለው ለአስተዳደር ግዛትና ተሪቶርይ የኢኮኖሚ ልማት መምሪያ እና በሥራ ችሎታ ለመጡ ማይግራንት ስለ መንግሥት ንግድ ሥራ መረጃ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ለሚረዱ ድርጅቶች መረጃን አውጥቶ ሊሰጥ ይችላል።

### ስልጠናና ትምህርት

ግላዊ መረጃ ምናልባት ሊወጣ የሚችል:

- ለDFAT, ለኢንዱስትሪ መምሪያና ለትምህርት መምሪያ ሲሆን ይህም በአውስትራሊያ ውስጥ ስልጠና ወይም መማር ለሚፈልጉ ተማሪዎች ለመርዳት ነው
- በአውስትራሊያ የሰራተኛ ገብያ ስለታቀደ የሥራ ቦታ ይዘት ስለሚከሰት ማንኛውም ችግር በሥራና ሰራተኛ መምሪያ በኩል ይወሰናል
- በውጭ አገር ሙያ ችሎታ፣ ለአንዳንድ የቪዛ ዓይነት በትምህርት መምሪያና በተወካይ ባለሥልጣኖች በኩል ይመረመራል
- በጎልማሳ ማይግራንት/መጤ እንግሊዝኛ መርሃግብር የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ለሚያቀርቡ ትምህርት ተቋማት
- ለትምህርቲ አቅራቢዎች ህጎች የሚጠቀሙ መንግሥታዊ አካላት።

### ጤና

ለርስዎ ቪዛ ማመልከቻ ሲባል የቀረበን የርስዎን ወይም የቤተሰብዎን ጤና መረጃ ለመንግሥት ጤና ጥበቃ ድርጅቶችና ለህክምና አቅራቢዎች አውጥቶ መስጠት እንደሚቻል ይህም ቪዛውን ለመስጠት ጤንነት የተሟላ ከሆነ፣ ለጤና ምርመራ አስፈላጊነት መነሳት ካለበት፣ ወይም የህዝባዊ ጤና ችግርን ለመቆጣጠር አጥንተው እንዲወስኑ መረጃዎች ይሰጣል።

### ስደተኛ እና በሰብአዊ ርህራሄ ለገቡ እና በደንበር ዳርቻ መከላከያ

መምሪያው የስደተኛንና በሰብአዊ ርህራሄ የገቡትን እና በሰብአዊ ርህራሄ ሰፈራ አገልግሎት መሰረት ለነሱ ሃሳብ ለማቅረብ ኮንትራት ላደረጉ (ተግባራዊ ከሆነ) የአገልግሎት አቅራቢዎች ግላዊ መረጃን መምሪያው መለዋወጥ ይችላል።

ስለ ጥገኝነት ፈላጊዎችና የመከላከያ አመልካቾች ወይም የሰብአዊ ርህራሄ ቪዛ አመልካቾች በተመለከተ ያላቸውን ግላዊ መረጃ መምሪያው ለተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን (UNHCR) አሳልፎ መስጠት ሲችል የዚህ ዓላማም ለሰብአዊ ርህራሄ ወይም ለመከላከያ አመልካቾች ማንነታቸውን ለመለየት ነው።

እንዲሁም በማይግሬሽን ለሚቀርብ አገልግሎት ይረዳ ዘንድ መምሪያው ግላዊ መረጃን ለአለም አቀፍ ድርጅት አሳልፎ ሊሰጥ ይችላል።

### እስር ቤት

ስለ ኢሚግሬሽን እስረኞች በተመለከተ መምሪያው ግላዊ መረጃን አሳልፎ መስጠት የሚችለው:

- ከእስር ቤት ሌላ አማራጭ ቅንጅትን፣ ሰው ለሌለው ደካማ እንክብካቤ ወይም ህጋዊ ሞግዚትነት በእስረኝነት ላሉ የአካልና አእምሮ ጤና ጉዳተኛ ለሆኑ እስረኞች በተመለከተ የአስተዳደር ግዛትና ተሪቶርይ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች
- የኢሚግሪሽንን ስልጣን የሚገልጽና ወደ መገልገያ ለማስተላለፍ የአስተዳደር ግዛትና ተሪቶርይ ጠባይ ማረሚያ አገልግሎቶች
- ወደ ሌላ አገር ለማስተላለፍ የሚረዱ በውጭ አገር ሆኖ የአሰራር ሂደት አገልግሎት አቅራቢዎች
- ትምህርት ቤቶች፣ የህክምና ባለሙያዎችና የጤና እና የበጎ አድራጊ አገልግሎት አቅራቢዎች፣ ወይም ለርስዎ አገልግሎት የሚሰጥ ወይም እርስዎን ወይም ቤተሰብዎ እንዲወጡ ለመርዳት አማራጭ ሁኔታዎችን የሚያጠኑ ማይግሬሽን አማካሪዎች።

### የህጻናት ድህንነትና መከላከያ

የህጻናት እና/ወይም የህጻናት ወላጆች/ሞጉዚት/ተንከባካቢዎች ግላዊ መረጃ ሊወጣ የሚችለው ለህጻናት በጐ አድራጎትና መከላከያ ድርጅቶች፤ ለአስተዳደር ግዛት/ተሪቶርይ ፖሊሲ ወይም ሌላ ጠቃሚ የአውስትራሊያ መንግሥታዊ ድርጅቶች:

- በኢሚግሬሽን እስር ቤት እና/ወይም በማህበርሰቡ ውስጥ እንክብካቤንና ደህንነትን ለማቀናጀትና ለመቆጣጠር
- አላግባብ ስድብ ወይም ቸልተኝነት ከደረሰ ለማጣራት
- የጉዞ ቅንጅትና ሰነዶችን በቀላሉ ለማቅረብ።

በጉዱፍቻ ወደ አውስትራሊያ ከሚገቡ ህጻናት የተዛመደ መረጃ ለአስተዳደር ግዛትና ተሪቶርይ በጎ አድራጎት ድርጅቶች፤ ለአውስትራሊያ ጉድፍቻ ማእከል ባለስልጣኖች እና በአውስትራሊያ አገር ውስጥ ለጉድፍቻ ድርጅት አሳልፎ መስጠት ይቻላል።

### የጉዞ ሰነድ ለማግኘት ለኢምባሲዎች፣ ከፍተኛ ኮሚሽን እና ኮንሱላት የሚሰጥ መረጃ

ከአገር ለመውጣት ሲባል ቪዛ ተሰጥቶዎት ከሆነ ወይም በአውስትራሊያ ውስጥ ለመቆየት ህጋዊነት ከሌለዎት ከአገር እንዲለቁ ይጠበቃል። ህጋዊ የሆነ የጉዞ ሰነድ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካልያዙ ወይም ካላገኙ ታዲያ መምሪያው እርስዎን ወክሎ እንዲሰጥዎት ያመለክታል። ይህ እርስዎ እንዲወጡ ቅንጅት ለማድረግ እድል ይከፍታል።

የጉዞ ሰነድን ለማዘጋጀት አግባብ ያለው ኢምባሲ፣ ከፍተኛ ኮሚሽን ወይም ኮንሱላት ከመምሪያው የሚሰጠው አነስተኛ መረጃ ብቻ እንደሆነ ነው። በዚህ ሊካተት የሚችለው፤ የርስዎ ስም፣ አሁን ያለዎት የፓስፖርት ዝርዝር መግለጫ ወይም ሌላ የመታወቂያ ሰነዶች እና ዝርዝር አድራሻ ይሆናል።

### ዜግነት

ከግላዊ ማንነት መለያ ባሻገር መምሪያው ግላዊ መረጃን ሊሰጥ የሚችለው:

- የዜግነት ክብረ በአል ለማስተናገድ ሲባል ለአካባቢ የመንግሥት ምክር ቤቶችና ለሌሎች ድርጅቶች ይሰጣል
- ስለ አውስትራሊያ ክብር የቀረበን ማመልከቻ ለማመዛዘን በጠቅላይ-አስተዳዳሪ ጽህፈት ቤት እውቅና ያለው ጸሀፊ እና የጠቅላይ ሚኒስተር መምሪያ እና ለሚኒስትሮች ስብሰባ ካቢነት ይሰጣልል
- በአውስትራሊያ ማህበረሰብ ውስጥ አዲስ ዜጎች እንኳን ደህና መጡ ለማለት ለፓርላማ አባላትና ለአካባቢ መንግሥት ከንቲባዎች ይሰጣል።

### የማይግሬሽን ጥናት

ግላዊ የሆነ መረጃ በአሁን እና ቀደም ብለው ለነበሩ ደንበኞች ላይ ጥናት ለማካሄድ ይጠቅማል። ለፖሊሲ እና/ወይም ለፕሮግራም እድገት ምርመራና ጥናት በሚል ዓላማ ግላዊ መረጃ ለሌላ ድርጅቶችና በሶስተኛ አካል ኮንትራክት ላደረጉ ድርጅቶች አሳልፎ መስጠት ይቻል ይሆናል። በኮንትራተሮች ለምርመራ ጥናይ ሲባል አጠቃቀሙ የተወሰነ ስለሆነ ኩንትራቱ በሚያበቃበት ጊዜ ከጥቅም ውጭ እንዲሆን ይፈለጋል። በጥናት ላይ የተሰበሰበ ጥሬ መረጃ ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት መረጃው የማን መሆኑ አይታወቅም።

በተለያዩ የማይግሬሽን መርሃግሮች በቅርቡ ለገቡ እና ለአዲስ ሰፋሪዎች ለህዝብ ቆጠራ በተዘጋጀ ጥናታዊ ውጤት ላይ ትንታኔያዊ መግለጫ ለማካሄድ ሲባል ግላዊ መረጃን ለአውስትራሊያ ስታስቲክ ቢሮ አሳልፎ መስጠት ይቻላል።

ለሰፈራ እቅድ ማውጣት ወይም ለሰፈራ አገልግሎቶችን ለማቅረብ እንዲረዳ በቅርቡ ከመጡ ጋር የተዛመደ መረጃን ምናልባት ለአስተዳደር ግዛትና ተሪቶርይ ድርጅቶች ወይም ለማይግራንት/መጤ አገልግሎት ድርጅቶች መስጠት ይቻላል።

## ዋና የአለም አቀፍ ድርጊቶች

ለአውስትራሊያ መንግሥታዊ ድርጅቶች ማለት የአስተዳደር ግዛትና ተሪቶርይስ ድርጅቶችን ያካተተ ግላዊ መረጃ አሳልፎ መስጠት ሲቻል፤ ይህም በዋና የአለም አቀፍ ድርጊቶች እንደ ከፍተኛ የስፖርት ውድድሮችና ጨዋታዎች፣ በአለም አቀፍ የሚመራ በአስተዳደር ግዛት ስብሰባዎች፣ ማሕበራዊ፣ ባህላዊ ወይም በሃይማኖት መሰባሰብ ወይም ክብረ በዓላት በአለም አቀፍ ደረጃ መካፈል ይሆናል።

እንዲሁም የርስዎን ሁኔታ ለማቀናጀት ስሜት የማይነካ መረጃን መምሪያው ከአውስትራሊያና አለም አቀፍ ድርጅቶች እንዲሁም ከሌሎች አገሮች ጋር አብሮ መጠቀም ይቻል ይሆናል።

## ስለ የመምሪያ ግላዊነት ፖሊሲ መረጃ

የመምሪያ ግላዊነት ፖሊሲ በድረገጽ፡ https://www.homeaffairs.gov.au/access-and-accountability/our-commitments/privacy ላይ ቀርቧል።

በፖሊሲው የሚካተት መረጃ ስለ:

- በመምሪያው የተያዘን ግላዊ መረጃዎን እንዴት ማግኘትና ማስተካከል ስለሚችሉ
- ስለ ግላዊነት መረጃ ህግ መጣስና ለመምሪያው ቅሬታ አቅርቦት አሰራር ሂደት በተመለከት እንዴት ቅሬታ ማቅረብ እንደሚችሉ።

## ለውጭ አገር አስተናጋጆች ያለዎትን መረጃ አሳልፎ መስጠት

መምሪያው የውጭ ኢንፎርሜሽን ተክኖሎጂ/ IT ኮንትራክተሮችን በመጠቀም መረጃን ለማስተላለፍና ለመያዝ ሲሆን ይህም በውጭ አገር ያሉ አቅራቢዎችን ያካትታል።

በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ ግላዊ መረጃን በውጭ አገር ለሚገኝ አስተናጋጆች አሳልፈን መስጠት እንችላለን። ብዙ ጊዜ አስተናጋጁ የሚሆነው ከኖሩበት ወይም ከተነሱበት ወደዚህ ከተሳፈሩበት አገር ይሆናል (በነዚህ አገሮች ላይ በመቃወም ለመከላከያ ጥያቄ አቅርበው ከሆነና ለነዚህ ጥያቄዎች ግምገማው እስኪጠናቀቅ ድረስ እየጠበቁ ካልሆነ በስተቀር)። ይህም በቅድሚያ የተሳፋሪ አሰራ ሂደት እና የኤሌትሮኒክስ ቪዛ አሰራር ሂደት ለማቀናጀት ሲባል መረጃን ለአየር መንገድ ወይም ለጉዞ ድርጅት መስጠትን ያካትታል።

እንዲሁም መምሪያው ከአውስትራሊያ ጋር መረጃን ለመቀያየር ስምምነት ካደረጉ አገሮች ያካተተ ነገር ግን በዚህ ብቻ ያላቆመ ከተባበሩት መንግሥታት/ United States፤ ከዩናይትድ ኪንግዶም/ United Kingdom፤ ከካናዳ እና ከኒውዚላንድ ብቻ ሳይወሰን መረጃ ይለዋወጣል። በነዚህ መረጃ መለዋወጥ ተደርጎ ለባዮመትሪክስ (የማንነት መግለጫ) መለዋወጥ ሊኖር ይችላል።

ከርስዎ ግላዊ ማንነት መለያ ጋር የሚመሳሰል ካለ ታዲያ ያለዎትን የህይወት ታሪክ መረጃ፣ የጉዞ ቅጂ ወረቀትና ሌላ የመታወቂያ ሰነዶች ወይም በነዚህ ላይ ያለ የሆነ መረጃን፣ በኢሚግሬሽን ያለዎትን ፈቃድና በኢሚግሬሽን ታሪክዎ (ይህም የሆነ የኢሚግሬሽን ማጭበርበርና የተፈጸመ ወንጀል ሊያካትት የሚችል) እና ማንኛውም የወንጀል ፍጸማ መረጃ ካለ ታዲያ መምሪያው ያለዎትን መረጃ ማውጣት ይችላል።

የዚህ መረጃ ማውጣት ዓላማው በተመሳሳይ መታወቂያና ተመሳሳይ ጥያቄ ላይ በሌላ ድርጅቶች የሚታወቁ ከሆነ የርስዎን ማንነት መረጃ ለማረጋገጥ ይረዳል።

ከአገር ዳርቻ ውጭ ሆኖ የሰብአዊ ርህራሄ ወይም የመከላከያ ቪዛ ማመልከቻ የሚያስገቡ ከሆነ የሚወሰነው በተለይ ላመለከቱት አገር ጸረ-መንግሥት መሰረት በማድረግ ስለሆነ ታዲያ መምሪያው ያለዎትን መረጃ ለዚያ መንግሥት አሳልፎ እንድማይሰጥ፤ እንዲሁም እርስዎ አውስትራሊያ ውስጥ ካልሆኑ በስተቀር እና እርስዎ፡

- ወዲዚህ አገር ለመመለስ ከጠየቁ ወይም ከተሰማሙ፣ ወይም
- አውስትራሊያ የመከላከያ ለመስጠት ግዴታ ሆኖ ያልተገኘ ሰው ከሆኑ።

| | |
|---|---|
| *የሽፋን ገጽ* | **www.homeaffairs.gov.au** |
| *አጠቃላይ የመረጃ መስመር* | በስልክ ቁጥር **131 881** በአውስትራሊያ የስራ ሰዓት በመደወል ኦፕሬተር ያነጋግሩ (ከስራ ሰዓት ውጪ ደግሞ የተቀረጸውን ድምጽ በማዳመጥ መረጃ ያገኛሉ)። ከአውስትራሊያ ውጪ ከሆኑ ባቅራቢያዎ የሚገኘውን የአውስትራሊያ መልእክተኛ ጽ/ቤት (Australian mission) ያነጋግሩ። |



© COMMONWEALTH OF AUSTRALIA, 2020